# መሳሳት ያኮራልን?

## አስተያየት ለአቶ አንዳርጋቸው ፅጌ

አበበ ተስፋ

አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ችግር የገቡ ሰው ሆነዋል። በአንድ በኩል በለየለት ወያኔነት ይታማሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የኢሕአፓ ሰርጎ ገብ ብለው የሚጠረጥሯቸው አሉ። በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ሰፊውን ፀረ ኢሕአፓ ፀረ ዶክተር ታዬ ዘመቻ ያዘዙና እያቀነበባሩ ያሉት እሳቸው ናቸው ተብሏል። ሰውየው ራሳቸው ለውዝግቡ ያደረጉት አስተዋፅዖ ቀላል አይደለም።

ነገርን ከመቀስቀስና ይብልጥ ውዝግብን ከማጋበዝ አንፃር አቶ አንደርጋቸው ባለፈው ሰሞን በአሜሪካ በሰጡት ቃለ መጠይቅ ድሮ ፅፈውት የነበረውን "የአማራ ሕዝብ ከየት ወዴት" መፅሀፍ አሁንም አምንበታለሁ ከማለታቸው ሌላ ደግሞ ታትሞ ለህዝብ እንዲሰራጭ እፈልጋለሁም ብለዋል። ይህ እንግዲህ በእልክ ደረጃ ከተወሰደ ለወያኔ ለፈሰፈስ ይላሉ የተባሉት ሰውዬ በአሉታዊ ቢሆንም ወኔ እየገዙ ነው ሊያሰኝ ይችላል። ያው የተለመደው ከአፈርኩ አይመልሰኝ አልባሌ ጠባያቸው ከሆነ ግን አቶ አንዳርጋቸውን (የተበሳጨባቸው ፀሀፊ ጉድ አርጋቸው ያላቸውን) መገሰፅ መምከር ግድ ሊሆን ነው። በተለይ ሰውየው ኪል በተባለው የቅንጅት አንጃ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ አሁንም ያላቸው በመሆኑና ቅንጅት አሁንም በባሰ ንትርክ ውስጥ እየገባ ነውናም (የአቶ በድሩ አደምን ቃለ መጠይቅና የፕሮፌሰር መስፍንን ማስጠንቀቂያ ያጤኗል) የአቶ አንዳርጋቸው በዚያ በተወገዘ ፅሁፍ አሁንም አምናለሁ ንግግር በዝምታ የሚታለፍ ሊሆን አይችልም። በዚያ መፅሀፋቸው ይዘት አሁንም ሰውየው ካመኑበት አንዴት የቅንጅት አባል ሊሆኑ ቻሉ?

የአቶ አንዳርጋቸው የአማራ ህዝብ ከየት ወዴት መፅሀፍ ሰውየው የወያኔ ባለሰልጣን ሳሉ ለወያኔ አቅዋም የነበራቸውን ሙሉ ድጋፍ የሚገልጥ ነው። ሕዝብ በብሄረሰብና ክልል መከፋፈሉን ደግፈው የአማራው ሕዝብ በብሄር ደረጃ ተሰብስቦ እንዳይታገል ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊ ነህ ብለው "ያስጠቁትን" እነ ኢሕአፓን ያወግዛሉ። መፅሀፋቸውን ወያኔ ሊፅፈው የሚችል ነበር ብንል ይዘቱን በሚገባ መረዳት ይቻላል። በጊዜው ብዙ ፀሀፊዎች የአቶ አንዳርጋቸውን የተሳሳተ አቅዋም አውግዘውና ለወያኔ የሰጠትንም ድጋፍ ተችተው እንድነበር ይታወቃል። አቶ አንዳርጋቸውና የኢሕዴን–ብአዴን ጓዶቻቸው ለአማራው የቆሙለት ሳይሆን በወያኔ ተቀጥረው አማራው ላይ የቆሙበትና መረግም የሆኑበት ናቸው መባሉም የሚዘነጋ አይደለም።አቶ አንዳርጋቸው ነፃ ያልወጣ ነፃ አውጪ ብለው ሌላ መፅሀፍ ሲፅፉ ደግሞ በውስጡ ላለፈው አቅዋማቸው ግለሂስ በማቅረባቸው የመጀመሪያውን መፅሀፋቸውን ስህተት አምነዋል የሚል ግምት ነበር። ግን አልሆነም። የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች በአንድ ላይ ሊኖሩ አይችሉም ብሎ ሲጮህ የከረመው ወያኔ ለስልጣን ሲበቃ ብዙሀኑን ቀጥቅጦ ለመግዛት መከፋፋል ሰላለበትና ሀገሪቷንም ለክፍፍል አደጋ ማጋለጡ እምነቱ በመሆኑ በክልልና በብሄረሰብ ደረጃ ሕዝብን ከፋፍሎና ኢትዮጵያዊነትን ተፃርሮ እየወሰደ ያለውን እርምጃ ዛሬም እንደ ትላንት አቶ አንዳርጋቸው ከደገፉ ቦታቸው ከመለስ ዜናዊ ጎን እንጂ ለኢትዮጵያ አንድነት ቆሚያለሁ ከሚለው ቅንጅት ውስጥ አይደለም፤ሊሆንም አይችልም። የአቶ አንዳርጋቸውን የመጀመሪያ መፅሀፍ ለማሳትምም ገንዘብም ወረቀትም ደግም መባከን የለበትም።

አቶ አንዳርጋቸው ካፈርኩ አይመልሰኝ ማለታቸው ከማንነታቸው ጋር ያለውን ችግር ግልፅ ያደርገዋል። የማያውቁትን አወቅኩ ማለት እንደሚፈልጉት ሁሉ ሲሳሳቱ ደግሞ ማመን ውድቀትና ውርደት ይመስላቸዋል። በዚህ በጠራራ ፀሀይ ካፖረት አድርጎና በከረባት ታንቆ ሲሄድ አዋቂ የሆነ የሚመስለውን ዳዊ ተብዬውን ይመስላሉ። አቶ አንዳርጋቸው በጣም ስልጣን ይፈልጋሉ- ይህም ከዚህም ከዚያም መጠጋትን፤አቅዋም ማዘበራረቅን አስከተሎባቸዋል። የትብብር ለነፃነትና ዴሞክራሲ ተቺ ነበሩ--ዞር ብለው ደጋፊ ሆነዋል። ቀደም ብለው በቅንጅቱ ላይ የፃፉትን ሂስ ዛሬ የሚያስታውሱ አይመስሉም። አቶ አንዳርጋቸው ባይመስልባቸውም የፖለቲካ ዕውቀትና ተመክሮአቸው ውሱን ነው። በእውር ሀገር አንድ ዓይና መቸም አለ ። ግን በቂ ተመክሮ ጨርሶ የላቸውም። ኢሕአፓ ነበሩ ቢባሉም (ያው እንደ ዶክተር ብርሃኑና ሌሎች) በዚህ ድርጅት ተመክሮአቸው የአጭር ጊዜ ያውም የጠርዝ ነው። ስደት ሳሉም በፖለቲካ እንቅስቃሴና ተሳትፎ አይታሙም። ከወያኔ ጋር ከሰመሩ በኋላ ደግሞ ሳጠኝነትን እንጂ ሀገርን የሚጠቅም ትግል ሊማሩ አልቻሉም። አባዱላ ፖለቲካ ያውቃል? ባጫ ዳባሌ? ፖለቲካን ከችሎታና ዕውቀት አንፃር ክብደት ከሰጠነው ማለት እንጂ እንደ ወያኔ ጀሌዎች ፖለቲካማ ዘረኝነትን ለማወቅ ብዙም ችሎታ አይጠይቅም።አቶ አንዳርጋቸው በሰል ብለው፤አደብ ገዝተው፤ምሪቃቸውን ውጠውና የሕዝብን ፍላጎትና ታሪክ አጢነው ከመገፕት ይልቅ እንደ ሌላው ጥራዝ ነጠቅ ዳዊት ዮሐንስ በማያውቁት የሀገርና የሕዝብ ታሪክ ላይ አልባሌ መፅሀፋቸውን ሊያወጡ በቁ። ሕዝብ ወያኔ ሲላቸውና አንቅሮ ሲተፋቸውም ለምን ብሎ ከመጠየቅ ይልቅ ሕዝብን ወይ በአላዋቂነት (ራሳቸውን ልሂቅ ልሂቅ ዶክተር ዶክተር መባባል ከሚወዱት ገጥመዋልና፤አካል ሆነዋልና) ወይም በፈረደበት ኢሕአፓ ተደናግሮ ነው ወደ ማለቱ አዘነበሉ። አቶ አንዳርጋቸው ትንሽ ዕውቀት ለአደጋ ትዳርጋለች በተባለው

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

መሰረት አወቅኩን አስቀድመው ከሂስ በላይ ነኝ ስላሉ ሊታረሙም ሆነ ሊመከሩ አልቻሉም። ይህ ይታረም፤ምክርን ያድምጡ፤የተሳሳተ ፅሁፍዎን ውድቅ ብለውና ከሕዝብ ይቅርታን ጠይቀው ይገኙ መባል አለባቸው።

ይህን ምክር አልሰማ ብለው የወያኔ ሳጠኛና ከፋፋይ ፖለቲካ ዕፁብ ድንቅ ብለው ያቀረቡበትን ፀረ አማራ ፀረ ኢትዮጵያ መፅሀፍ ዛሬም አምንበታለሁ የሚሉ ከሆነ ግን ሰልፋቸው ከወያኔ ጎራ ነውና የሚመለከታቸው ክፍሎች ከጉያቸው አውጥተውና አባረው ወደ መለስ ዜናዊ ሳይውል ሳያድር እንዲልኳቸው መጠየቅ የግድ ይሆናል። የአቶ አንዳርጋቸው ቦታ ለኢትዮጵያ አንድነት ከሚሰለፉት ጎን ሳይሆን ከወያኔዎቹ ጋር ነውና።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com